# የኢትዮጵያ ሚለንየም በዓል

(ከማህሌ በቀለ)

ይህ ጽሑፍ እስከወጣበት ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊከበር የሚታሰበው የ2000 ዓመተ ምህረት በዓል 273 ቀን ይቀረዋል፡፡ ይህ በዓል እንዲከበር የወሰነው ማነው? ለምንስ ማክበር አስፈለገ? በዓሉንስ ከማክበር ምን ይገኛል? በዓሉስ እንዴት ነው የሚከበረው? እነዚህና ተመሳሳይ ጥያቄዎች በኔ ብቻ ሳይሆን በብዙ ኢትዮጵያውያን አዕምሮ ውስጥ ሳይጉላሉ አይቀሩምና ደጋፊም ሆነ ነቃፊ ቢኖር የመሰለኝን ልተንፍስ፡፡

እስኪ 100 ዓመት ያህል ወደኋላ እንሂድና ከ1888 እስከ 1928 ኢትዮጵያና ሕዝቧ ምን ይመስሉ እንደነበር በአጭሩ እንመልከት፡፡ ይህ ጊዜ ኢትዮጵያ ጣሊያንን ድል ያደረገችበት፣ ዘመናዊነት የተጀመረበት ማለትም ባቡር፣ መኪና፣ ስልክ፣ ሆቴል፣ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታልና የመሳሰሉት ላዕላይና ታዕታይ መዋቅሮች መዘርጋትና መስፋፋት የጀመሩበት ወቅት ነበር፡፡ ኢትዮጵያም ረዘም ላለ ጊዜ ሰላምና መረጋጋት ያየችበት፣ ኢትዮጵያዊነት የሚኮራበት፣ ኑሮም ቢሆን በገጠርና በከተማ እርካሽ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ ብዙ ፖለቲካ ውስጥ መግባት አልፈልግም ነገር ግን የታየውንና የተሰማውን ነባራዊ ዕውነት ማውሳት ይቻላል፡፡ ሆኖም ደግሞ ይህ ዝርዝር ለሌላ ጊዜ ይቆይ፡፡

ኢትዮጵያ ከአፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንግሥት በኋላ እስከ 1999 ድረስ ሦስት መንግሥታት የገዟት ሲሆን በመጨረሻ የደረስንበት የእድገት፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ደረጃ የሚያሳዝንና የሚያስተክዝ እንጂ ድግስ ደግሰን ፈንጠዝያ የምንልበት አይደለም፡፡

ዛሬ በኢኮኖሚው ደረጃ በአለም ውስጥ ከ174 አገሮች 170ኛ ሆነናል፡፡ ድህነት ቤቱን የሰራብን ሰዎች ነን፡፡ ባለፉት 33 አመታት እንኳን ድርቅ 3 ጊዜ መቶን በረሀብ አልቀናል፡፡ አሁንም በሰው ሰራሽ ጠኔ እያለቅን ነው ያለነው፡፡ ታዲያ የትኛው የጥጋብ ዘመን ነው የሚከበረው፡፡ በዚህስ ድግስና በዓል ላይ ደሀና ረሀብተኛው ኢትዮጵያዊሰ ይጋበዝ ይሆን? ባይጋበዝም እንዲያው ባለበት ቦታ ሆኖ እንዴትና ምኑን ነው የሚያከብረው?

በማህበራዊው ኑሮ ደግሞ ሥራ አጥነት፣ ስደት፣ ቀሳፊ በሽታዎች፣ የባህል ብክለትና የመሳሳሉ ችግሮች ህዝባችንን እያረገፉትና እያዘቀጡት ይገኛሉ፡፡ ታዲያ የቱን ጥሩ ስራችንን ነው የምናከብረው? ወጉ አይቅር ካልተባለ በስቀር!

የፖለቲካውማ አይነሳ፡ የቀረው ቀርቶ እንዲያው ካለፈው የግንቦት ምርጫ ወዲህ ያውልህ የዲሞክራሲ መብትህ የተባለው ሕዝባችን አይደል እንዴ የወያኔ ሰለባ የሆነው፡፡ በዘረኛውና በአምባገነኑ የአቶ መለስ አገዛዝ የሞተው፣ የጠፋው፣ የተደበደበው፣ የታሰረው፣ የታፈሰው፣ የተሰደደው፣ ከሥራ የተፈናቀለው፣ እንዲህ በአጭር ጊዜ ተረስቶ ነው እኛ የ2000 ዘመንን በዓል የምናከብረው? እንዴት ነው ጎበዝ እናስብ እንጂ፤ ህሊናኮ የተፈጠረው ለዚሁ ምክንያት ነው፡፡ በዚሁ በተባለው ቀን አዲስ አበባ ሄደን መንግሥት ከሥልጣን እንዲወርድ ሠላማዊ ሠልፍ እናድርግ

የምንል ከሆነ ጥሩ አለበለዚያ ግን በጎስቋላው ደሀ ሕዝብ ላይ ዶላራችንን መንዝረን ልንፎልልበት አስበን ከሆነ ይህ ጭካኔ ነው፡፡ ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንምና ለጊዜው ይህ መንደርደርያ ሃሳብ ይሁንና በዚህ በዓል ላይ መገኘት የፈለጋችሁና ያሰባችሁ ከህሊናችሁ ጋር ተማክራችሁ መደረግ ያለበትን ትክክለኛውን ነገር አደርጉ ኋላ ፀፀትና ተጠያቂነት ይመጣልና፡፡ ይህ በዓል ተሳክቶለት እንኳን ቢከበር አዲስ አበባ በሸርአተን ሆቴልና አካባቢው ሊታዩ የሚችሉት የኢሕአዴግ ሰዎች፣ የዋህ ሀብታሞች፣ ሆድአደር ብልጦችና ግድ የለሾች ይሆናሉ እንጂ ይህ በዓል ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትርጉም የለሽና ፌዝ ነው የሚሆነውና ከታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ጉዳዩን በንፁህ ህሊና ተመልከቱት፡፡

- ሚልዮን ህፃናት ያማቸውን በሚዉልቡትና በሚያድሩበት አገር
- ሚልዮን ኢትዮጵያውያን በHIV/AIDS በሚረግፉበት አገር
- ሚልዮን ኢትዮጵያውያን ሥራ አጥ ሆነው መኖር ባልቻሉበት አገር
- ሚልዮን ኢትዮጵያውያን ለቁራሽ እንጀራ ለማኝ በሆኑበት አገር
- የብዙ ሚልዮን ኢትዮጵያውያን የነፃነት ህልም በተጨናገፈበት አገር
- የብዙ ሚልዮን ኢትዮጵያውያን ድምፅ በተሰረቀበት አገር
- ለዴሞክራሲና ለሠላም የቆሙ ሠላማዊ ኢትዮጵያውያን በመለስ የአጋዚ ጦር በጭካኔ በተረሸኑበት አገር
- የህዝብ ተመራጮችና ለውጥ ፈላጊዎች በቃሊቲ እስር ቤት ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ በሚማቀቁበት አገር
- ብዙ ሽህ ኢትዮጵያውያን በግፍ በተደበደቡበትና በታፈሱበት አገር
- ጭንቀት፣ ሥጋት፣ ፍርሀት፣ ስደትና ተስፋ መቁረጥ በነገሱባት አገር
- ጠባብ፣ ዘረኛ፣ አምባገነናዊና ፀረ ኢትዮጵያ መንግሥት ባለበት አገር
- ኢትዮጵያዊነት መለያችን አደጋ ላይ በወደቀበት አገር

በኔ ሚዛናዊ አመለካከት ይህ የ2000 ዓ.ም. የሚለንየም በዓል ጉዳይ በታሪካችን ላይ ጥቁር ነጥብ የሚጥል፣ ለህዝባችን አለመቆርቆራችንን የሚያሳይና ለአገራችንም ግድ የለሽ መሆናችንን የሚያመለክት ሊሆን ይችላልና በዚህ ህሊችንን ሠላም ሊያሳጣ በሚችል ተግባር ውስጥ ከመሳተፍ ይልቅ በምትኩ ....

በዚህ በዓል ላይ የምናጠፋውን ወጭ 10% ወይንም የፈቀድነውን መጠን ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች በመስጠት የተራቡትን፣ ጋዜጣ ለብሰው ጎዳና የሚያድሩትን፣ የታመሙትን፣ በስደት አገር ላይ የሚሰቃዩትንና የተመሳሳይ ቀውሶች ሰለባ የሆኑትን ወገኖቻችንን እንርዳ፡፡ በተጨማሪም አገራችንን ከረሀብ ወደ ጥጋብ፣ ከኋላ ቀርነት ወደዘመናዊነት፣ ከወገናዊነት ወደእኩልነት፣ ከአፈና ወደ ነፃነት፣ ከሽብር ወደ ሠላም፣ ከአምባገነንነት ወደ ህዝባዊነት ሊያመጣ የሚችልን ዴሞክራሲያዊ ትግል እንደአቅማችንና ችሎታችን እንደግፍ፡፡ በዚህ ምስቅልቅል ባለ አላፊ ህይወት ውስጥ የማያልፍ ሥራ ሰርቶ ማለፍ ሰብአዊ ጥበብ ነው፡፡

**ሠላም፣ ነፃነት፣ ፍትህና ዴሞክረሲ ለኢትዮጵያ!**